# ማነህ ባለሳምንት? የ “መሪ” ወርተራ

አስፋ ጫቦ

**December 10, 2016**

እንደመግቢያ
የኦርቶዶክሶች ማህበር ቤት ወርተረኛውን ለመመደብ ዳቦ ከተቆረስና መውጫ ሲቃረብ ሙሴው ይነሳና፡
ማነህ ባለሳምንት?
ያስጠምድህ ባስራ ስምንት
እኔነኝ የምትል የቅዱስ ገብርኤል ወዳጅ ይላል።

ገብርኤሉ እንደማኅበራቸው ታቦት ሥም የቅያየራል።ተራኛው ይቆምን የሚባለውን ብሎ ጽዋውን ይረከባል።ይህ እውደት በየወሩ ቋሚና ቀጣይ ነው።ከልጅነቴ ያስታወስኩት ነው። እዚህም
ማነህ ባለሳምንት?
እኔነኝ የምትል ሴራ ወዳጅ ማለት የሚቻል ይመስለኛል።
ማኅበሩ ወርሐዊ ነውና በየወሩ ተረኛው ደጋሽ ቤት ይሔዳል።በፓርቲዎች ውስጥ ያለው ሹምሽር የዚህ አይነት ባሕርይ የሚያጣ አይመስለኝም። ግቡ፤መንፈሳዊነቱና፣አለማዊነቱና ሰለማዊነቱና ሴራነቱ እንደተጠበቀ ሆኖነው።

የምጽፈውን የምጽፈው ብልጭ ሲልብኝ ወይም ሲልልኝ ነው። አብዛኛው!እንጅ ይህንን እጽፋለሁ፤በዚህ ጉዳይ ላይ እጽፋለሁ የሚል እቅድ ኖሮኝ የሚያውቅ አይመስለኝም።ግብታዊነት የሚሉት ሥር የምመደብ ይመስለኛል።ይህም የተጻፈው በዚሁ አይነት ነው።

ማህበራዊ ገጽታዎች በተለይም Facebook ትልቅ ትምህርት ቤት ሆኖኛል።አገር ተሰብሶቦ ሲያወጋ የሚያድርውንና የሚውለውን ማዳመጥ፣አንዳንዴም በወጉ ውስጥ ወጣ-ገባ ይመጣል። Facebook ከገባሁ ሁለት አመት ሁኖኛልና ::"እንኳን ደስ ያለህ!" መልእክት አንድ ቀን ይህንኑ ከ Facebook አግኝቼ ሳኩኝ። እኔ የማላስታውሰውን አስታውሶ የሚነገርኝ "ወዳጅ"ም አለኝ ማለት ነው።

አገር ተሰብስቦ ያወጋል ብያለህ። አገር ደግሞ ሰፊ ነውና ብዙ ነገር ያቅፋል።ከዚህ ውስጥ ጥሩ፤ መጥፎ፤አስጸያፊም አለ።ፈርንጅ The Good,The Bad, and the Ugly እንዲል! "ሆድ ከአገር ይስፋል!" ብሎ መጓዝ ነው። ወይ እንደፈርንጆቹ "ልዩነታችን ለዘለዓለም ይኑር!" (Vive la difference!) ብሎ መቀጠል! ነው።
እንግዲህ "የሀሳብ ልዩነት" ሲባል "ጤናማ ልዩነት!" መለቴ እንጅ አጸያፊውም "ለዘለ አለም ይኑር!" ማለት አይመስለኝም! እንደኔ እንደኔ አስጸያፊው አንድም ቀን አይደር!የ Facebook ነገር ጥሩ ነው። አስጸያፊው ተመክሮ ተዘክሮ የማይመለሰ ከሆነ ለማሰናበት 30 ሴኮንድ በቂ ነው ነው ።"ከዚች ሴኮንድ ጀምሮ 'ወዳጄ'አይደለሽም፤አይደለህም!" ማለት ይቻላል። "Unfriend!" ይለዋል። "ተፋቱ!" ማለት ነው። በዚሁ መሠረት መከሬ- ዘከሬ እምቢ ያሉኝን ጥቂት "ፈተቼ" የለቀቅኳቸው አሉ።
የአሁኑጉዳይ

Facebook ከገጠምኩ ሁለት አመት ሆኖኛል ብያለሁ። ትምህርት ቤትም ሆኖኛል ብያለሁ።ከልቤ ነው! 5,000 ወዳጆች(Friends) አሉኝ! ብዙዎች ወዳጅ ሊሆኑ ጠይቀውኝ በ Facebook "ያለህ ይበቃል!' ስለተባልኩ አልጨመርኳቸውምና በዚህ አጋጣሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ወዳጆቼ በአብዛኛው ወጣቶች ናቸው።በአብዛኛው ያሰኙኝን እንደነፐሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የሉ አዛውንቶችም ስለአሉበት ነው።

የዚህ የኔ "ወጣት ወዳጆቼ" ነገር ይገረመኛል። ሁሉም ማለት ይቻላል "አንተና ጋሼ አሰፋ!" ነው የሚሉኝ። ልጆቼ አድርጌ ነው የምወስደው!ልጆቼም የልጅ-ልጆቼም "አንተ" ስለሚሉኝ!።እነሱ "አሴ!" ነው የሚሉኝ። እዚህም አሴ የሚሉኝ ጥቂት አሉ። አንድ አገር ሙሉ፤አለም ሙሉ ቤተሰብ ያለኝ መስሎ ይሰማኛል! ደስ ደስም ይለኛል!። ጥያቄ ይጠይቁኛል። መልስም እሰጣለሁ። "ይህን አድርግ/አታድርግ"ም ይመኩሩኛል።አንዳንዴ ወይይታቸውም ጫወታቸውም ውስጥ እገባለሁ። ሰሞኑን በተለየም ልደቱ አያሌውን ባንድ በኩል ሰማያዊፓፓርቲ በሌላው አድረገው ሲወያዩ ገባሁና አስተያት ሰጠሁ።
የመጀመሪያው አስተያየት ይኸውና።

እኔ ከብዛታቸውም ይሁን የሚሉት በደንብ ስለማይገባኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች ላይ ምንም ከማለት ተቆጥቤ ኖር ኩ። የዛሬ ሁለት ይሁን ሶስት ወርበፊት ዶክተር መረራ ጉዲናና የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀ መነንበር እዚህ አሜሪካ መሆናቸውን ሰማሁን ለ ሁለቱም ደውልኩላቸው። መረራን አውቀዋለሁ።ይልቃልንአላውቀውም።ሁለቴ መስለኝያነጋገርኩት።ማነጋገር ከማለት ያዳመጥኩት ማለትይሻላል። ብስለቱ፤ጥልቀቱና እርጋታው በጣም ገርሞኝ በርታ! ተባረክ!አልኩት።
ለለላምታና በርቱ ለማለት ብቻ ነበር የደውልኩት። ወዲያውኑ ወረደ፤ይበሉ ተሻር ወይም ተባረረ የሚል ስምቼ "አይ የኛ ነገር!" ብዬ አዘንኩ።

አሁን ከኢዴፓ ጋር የሚባለው በሙሉ አይገባኝም። ዝርዝር መረጃ ስለሌለኝና ምናልባትም እንዳይኖረኝ ስለፈልኩም ሊሆን ይች ላል። የማይሆን ነገርበሰማሁ ቁጥር ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ያመኛል።ውስጤን!ኢዴፓ ልደቱ ያለበት ከሆነ ባለፈው አንድ ስብሰ ባ ላይ ልደቱ ሲናገር የሰማሁን የመንግስት ወኪል ወይ ቃልአቀበያየሚመስልጠረንነበረውልበል?
እኔ ምን አውቃለሁ!
ሁለተኛም አስተያየት ስጥቻለሁ።
በሁለተናኛው እኔን በግልም የሚነካ ተነስቶ ነው።
ይኸውናበዚህ ዙሪያ የሚደረገውን ውይይት፤በተለየም የጋላታ ጋሞና የኤደን መኮንን ተሰማምቶኛል!"የሠለጠነ ውይይት ወይም የሀ ሳብ መለዋወጥ" Civilized Discourse) መስሎ ታይቶኛል።

ከዚያ በፊት ግን ስለእኔ መጀመሪያ ከደርግ ጋር የነበረው ግንኙነት! እኔ የነበረኝ ግንኙነት ያ "የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ነው! " ብዬ ሙሉ ለሙሉ አምኜበትነው። ነውም!!የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዘመናት ባርነት ነጻ አውጥቷል። ኢትዮጵያን ሬፑብሊክ አድርጓል ።ከዚያ በኋላ በዋናነት በአመራር፤በተለይም በመንግስቱምክንያት አስቃቂና አሳዛኝ በደል በኢትዮጵያ ሕዝብ፤በተለይም በወጣቱ ላይ ተፈጽሟል። ለዚያም ተጠያቂና ናቸው የተባሉት ዋጋውን በእስራት ከፍለዋል።ፋይሉ አንድ ቀን አንድ ቦታ መዘጋት ያለበት ይመስለኛ ል። ያለበለዚያ ሁሌ ሙሾ ያወርድን እንደሁ የአሁኑን ያስተናል ብዬ እፈራለሁ።

በተለየ እኔን በሚመለከት!ከተወሰነ ቀን በኋላድጋፌን አቆምኩ። ይህንኑ "የኢትዮጵያ አብዮት ከየት ወዴት? ትላንት፤ዛሬናነገ ! "የሚል ወደ 30 ገጽ የሚድረስጽፌ አሰራጨሁ።ነጻነት ቅጽ 1 ቁጥር 1! ለዚያም ወደ 11 አመት ታሰረኩ።ያ ፋይሉን የሚዘጋልን መ ስለኝ።

ልደቱን በሚመለከት በ 97 ምርጫ ሰበብ በሚደረገው ሁካታ ምክንያት email ሁሉ ተለዋውጫለሁ።እስቲ ለምትከሱቱ ማስረ ጃ አቅረቡ? ብዬምየጻፍኩይመስለኛል። ስለዚህ የልደቱን ጉዳይ የማየው በጅምላ መልክ አይደለም ለማለት ነው።
ያኛውን ወይም ይህኛውንድርጅት ለምን አትደግፍም ?ለተባለው ሲመች "አንተም ተው!አንቺም ተይ!"የሚል ሽማግሌ ያስፈልጋል በ ሚል ምክንያትትይመስለኛል።

ይህ "የሰለጠነ ውይይት" ጥሩ ነው፣ አድማሱን ሰፋ ብታደርጉትጥሩ ይመስለኛል። ሰፋ ማድረግ ማለት ይህ እርስ – በርስ መባላት በ 97 ምርጫ ጊዜም ሆነበደርግ ዘመን ያደርገውን አይቶ ዘለቄታው ምን ይመስላል ? የሚል አንጻር መጨመር ማለት ነው።

ስለ ልደቱ አሁን የሰጡሁት አስተያየት በውይይቱ ላይ የሰጠውን አስተያየት ጠረኑን ስለ አልወደድኩት ነው። "መስሎ ማታየት" ሌላ ትርጉም መስጠቱ ያለነውና ! Pereception is Reality የሚሉት!

እዚህ ከላይ

በለጠፍኩት "..እኔ ከብዛታቸውም ይሁን የሚሉት በደንብ ሰለማይገባኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች ላይ ምንም ከማለት ተቆጥቤ ኖርኩ።የዛሬ ሁለት ይሁን ሶስት ወር በፊት ዶክተር መረራ ጉዲናና የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀ መንበር እዚህ አሜሪካ መሆናቸውን ሰማሁን ለሁለቱም ደውልኩላቸው።መረራን አውቀዋለሁ።ይልቃልን አላውቀውም..."በሚለውልጀምር መሰለኝ ልውቅ እንኳ ብል ለማወቅ የሚያስቸግር ይመስለኛል። "ዘጠና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሥርተዋል ይሁን ተፈልፍለዋል" የሚል ነገር ያነበብኩ ይመስለናኛል።በጥንቃቄ ነው ያማበነው! ጥንቃቄው ለአገሬ ብቻ አይመስለኝም። ለጤንነቴም ጭምር ይመስለኛል። ጠለቅ ብየ ለማውቅ ብፈልግ፤ የሚጠለቅበት ጥለቀትአለው ብለን ብንገመት እንኳ፤መንፈሰን የሚረብሸው ይመስለኛል። ለመሆኑ ምኑ ነው መንፈስ የሚመረበሸው?ወይም ሊረብሸው የሚችለው?

ጥሩ ጥያቄ ነው! ዘጠና ፓርቲዎች ተመሠረቱ ተባለ። ለዘጠና ፓርቲ የሚሆንየፖለቲካ ጽንሰሐሳብ (Theory)ከየት ሊመጣ ነው? ሁሌም፤አሁንም ያለው የፖለቲካ አስተሳሰብ የቀኝ ፖለቲካ፤የመሀል ፖለቲካና የግራ ፖለቲካ ነው።እርግጥ "ጽነፈኞች"(Extrimists ) የሚባሉ የግራም የቀኝም አሉ። ጽንፈኞች ቁጥራቸውም ተሰሚነታቸውም ከቁጥር የማይገባ ስለሆነ "ጤና-ያጡ ግለሰቦችመሰባሰቢያ" ተደርጎ ይወሰድና የሚያተኮርበት የለም። የሚተኮረበትም አይደለም። እርግጥ ዛሬ ያለፈ በደል ክምር ገንፍሎ ፤የሐይማኖት ሽፋን ሁሉ ወስዶአስፈሪ ሆኗል። ያም ቢሆን ያው ጽንፈኛ ናቸው። አሁን በፈነዳው የሕዝብ ቁጣ ሳቢያ ዛሬ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ "ጽንፍና መሀል" መለየት አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ሳያስፈልግ የሚቀር አይመስለኝም።

አንዱ ይህ የመስለኛል ገሸሽ እንዲል ያደርገኝ። "ዘጠና ድርጅቶች"የሚባል ነገር ሊኖርአይችልም ኮ የለምኮ! አይገባምኮ! "በአንድ አፍ ተነጋገሩ ወይም መነጋገር ትችላላችሁ!" ብሎ፤መከሮ፤ገስጾ፤ተማጽኖ ማቀራረብ ለኔም ሆነ እንደኔ ላለው ተራ ተርታ ሰው( The average person)ከባድ የቤት ሥራ ይመስለኛል።

ሌላውየታየኝ ችግር "እሽ ዘጠና ሁኑ! ለመሆኑ ልታሳፍሩን የምትፈልጉት አህያ፤ በቅሎ፤ ፈረስ፤ ጋሪ፤ ታኪስ ፤አውቶቡስ፤ባቡር፤ አውሮፐላን ወይምመርከብ የትና ወዴት ሊወስደን፣ ሊያደርስን ነው?" የሚለው ጥያቄ ገልጽ አይደለም።ለኔ አይደለም!ላማችን፤ግባችን፤አድማሳችን የማያሻማ የተማረ የተመራመረውም ሆነ ከተሜው፤ገጠሬው ወጣት ሽማግሌ አስተርጓሚ ሳይፈልግ መረዳት የሚገባው መሆን አለበት። መልእክቴ ግልጽ ካልሆነ የሰሚው፤የአድማጩ ችግር አይመስለኝም። የተናጋሪው፣የአቅራቢው እንጅ።

ሌላው ድፍን አገር የሚያውቀው ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት የሚሰጠው ይመስለኛል። ወያኔ በሉት ኢሕ አ ደ ግ እቡይ መሆኑየአደባባይ ሚስጥር ነው። ዛሬ ሳይሆን ሕዝቡ ከግንቦት 1983 ጀምሮ የሚያውቀው ነው።እዚያ ላይ ብርቱ ጊዜ የሚባክን ይመስለኛል ከዚህ ጋር አብሮ የሚሔደው ክስና ውቅስ፤ዛሬም ያልተቋጨው "ይኸኛውወያኔ ሰርጎና አስርጎ ያስገባው ግለሰብ ነው ፤ድርጅት ነው "የሚለው ጣት መቀሰርነው።የአስርጎ ማስገባትነገር አለም አቀፋዊ መሆኑንም ባላውቅም በየአገሩ የነበረ፣ያለ፤የሚኖር

ነው።

እዚህ አሜሪካም አለ። በቅርቡ እንግሊዝ አገር በዚሁ ጉዳይ የሌበርና የኮንስርቫቲቭ ፓርቲ ይሁን ሌላ ሲካሰሱ ነበር። ይልቅስ የሚደንቀው ወያኔ ሰርጎ ወይም አስርጎ ባያስገባ ነው። "ወያኔ እንዲህ አድርጎ እንዲህ ሆንን" ማለት ወይኔ በፖለቲካ ጥበብ፤ተክኒክና ታክቲክ ይበልጠናል፤በልጦናል ብሎ እንደማመን ይመስለኛል። ቡሐቃዋን በቅጡ አትክድንምና ሁሌ በድመቷ ወይም ውሻው ላይእንደማታማርረው የቤት እመቤት የሚመስልነገርያለው ይመስለኛል።በሩን ሊዘጋ የሚችለውን ያክል መዝጋት ነው። ካልተቻለ በዚያም ይሁን በዚያ ለዚህ የጨዋታ ሜዳ በቁ ሆኖ አለመገኘትንም የሚጠቁም ይመስለኛል።"ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው!"ንም አውቃለህ
ሴራው

የ 1997 አገር አቀፍ መርጫ ውጤትና ያንን ተከትሎ ተቃዋሚ ፓርቲ ነን የሚሉት ያደርጉት አልገባኝም።ሊገባኝ የሚችልም አይመስለኝም። ያንን በሚመለከት በወቅቱ ተዋናኝ ከነበሩት አንዱን የተቃዋሚ ድርጅት መሪ በስልክ ለማነጋገር ሞክሬ መልስ አላገኘሁም። የሚመስል መልስ አላገኘሁም ማለት የሚሻል ይመስለኛል። ምርጫውን አሸነፉኮ!በአገር አቀፍ ደርጃ ከ 200 በላይ መቀመጫ ያገኙ ይመለኛል። ያም ይቅር አዲስ አበባን፤የኢትዮጵያን ዋና ከተማ፤የአፍርቃን ዋና ከተማ፤የተባበሩት መንግስታትን ዋና ከተማን ሙሉ ለሙሉ አሸነፍኮኩ!ገቢናው መሪው ፤ሹፌሩ(The Driver's Seat)ያለውኮ አዲስ አበባ ከተማ ነው! ለኔ ማመን የተሳነኝ ድል ነበር።

ከምርጫ በኋላ በአብዛኛው አውዛጋቢ ጥያቄ ይነሳል። የትም ሁሌም ያለ ጥያቄ ነው።ውዝግቡን ለመፍታትም የታወቀና የተረጋገጠ የሌሎች አገሮች ተመክሮም አለ። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያንን የተጠራቀመ ልምድ አልተጠቀሙበትም። ሊጠቀሙ አልፈለጉም ወይም ከነአካቴው አያውቁትም ማለትም የሚያስችል ይመስላል።የሚያማርሩበት ነገር እንኳቢኖር፤ በኔ አስተያየት፣ ይህን ያክል የሚያማርር ነጥብ የነበር አልመስለኝም ፤የታወቀው" ብልጥ ልጅ የሰጡትን እየበላ ያለቅሳል!" የሚለው መመሪያ እንደ ሀ ሁ ማታወቅ የነበረበት ይመስለኛል። የወሰዱት አማራጭ ትላንትና የመረጣቸውን ሕዝብ "እስቲ ፓርላማ እንግባ አንግባ!?" ምን ይመስለችኋል !?"ብለን እንጠይቅ የሚል ነበር። ውጤቱ "የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች!" ሆነ። በብዙ ሞቶ የሚቆጠር ሕዝብ ለሞቶ ተዳረገ። መሪዎቹ የተባሉት ከርቼሌ ወረዱ። "አስታራቂ ሽማግሌ!" የሚባሉ ከመለስ ዜናዊ ፋብሪካ ተፈለፈሉ። መሪዎቹ መለስ ዜናዊን ይቅርታ ጠይቀው ተፈቱ። ያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያንን ሁሉ ጥይትና ዱላ ችሎ ተአምር በሚመስል መንገደ ያገኘው ድል ከንቱ ሆነ። ለዚህ አይነት ክህደት እንኳን ባይባል አላአዋቂ ሥራ ተጠያቂ፤ተጠያቂው(ዎች) ማነው? እነማናቸው? የሚለው መልስ ያገኘ አይመስልም። ከሆነም እኔ አልሰማሁም። አንድ አርግጠኛ ነገር አለ። ወያኔ ዘላቂ ትምህርት፣"ይህችን ስህተት አንደግማትም!" የሚል ትምህርት አግኝቶ ተግባራዊ አድርጓል። የምርጫውን በር ዘግቶ ቁልፉን ወረወረው !የተቀረነው የተማርንበት አይመስለኝም።

ሌላ ተያያዥ ጥያቄ መጠየቅም የምንችል ይመስለኛል። ወያኔ የተማረበት የሚመስለውን ዞር ብለው ሲያዩት ጊዚያዊ ይመስላል።ባሰበት እንጅ አልተማረበትም። ዛሬ የውስጥ አውቂዎች ነንየሚሉእንደሚነግሩኝ (ለነገሩ የማናውቀው ውስጥ ያለ ይመስል) "ብትፈልግ ወያኔ ፤ብትፈልግ ኢሕአደግ በለው የሚባል ነገር የለም።ተከስክሷል! ጥላው ነው ያለ የሚያስመስለው።እያንዳንዱ የ ኢሕ አ ድ ግ አካል አምሳል ነኝ ተብዬው ውስጡ ሶስት ወይም አራት ብታ ተፈረካክሶ የለመልሕቅ ይዋዥቃል" ነው የሚሉኝ። በእርግጠኝነት ያላቸው ነገር ቢኖር አፈሙዙ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚባሉት ያው የዛሬ ስንተስ አመት ሲሰሩት የነበረውን ያንን የውስጥ አድማ እንበለው ሴራ ቀጥለዉበታል።ትላንትን ዛሬ አድርገውታል። ይህ፤ለዚህ መነሻ የሆነኝ

የኢዴፓና የሰማይ ፓርቲ በአደባባይ መናቆር ትላንት አሁንም ትላንት ሳይሆን ዛሬ መሆኑን የሚያሳይ ይመስለኛል።

እንዳልኩት እኔ የአሁኑን ድርጅቶችም ሆነ መሪዎቻቸውን አብዛኞቹን አላውቅቸውም። ዶክተር መረራ ጉዲናን አውቀዋለሁ።ቢያሰሩት "ኤረእባካችሁ ፍቱት!"ብዬም ጽፍያለሁ።ዶክተር በየነ ጴጥሮስን ትንሽ የማውቀው በአብዛኛው  የማላወቀው ይመስለኛል። የዶክተር በየነ ስም ሲነሳ ሱዘን ሳረንደንን (Susan Sarndon 1995)ያስታውሰኛል። የዛሬ ስንትስ አመት (1995)Dead Man Walking  የሚል ፊልም ውስጥ ዋንናዋ ተዋናይ ነበረች። "በቁሙ የሞተ!" እንደማለት ነው። በቁሙ ሞቶም ሙቱ ሰውም ግና ነፍሱ አልወጣታችምና ፊልሙ ውስጥ ይታያል።እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ፊልም ነበር።ዶክተር በየነን የሚመሳሰልብኝ ያንን ሁሉ ድርጅት፤በተለይም የደቡብን ሕብረት ቀብሮ፤አባላቱን አሳዶ ዛሬምእዚያው መኖሩ ነው። ልጅ ሆኜአ ጨንቻ መሰለኝ የሰማህትን የልጆች ዘፈንም አስታወሰኝ።" እዚያ ነሽ ዛሬም እዚያው ነሽ? አስሮ የሚገርፍሽ ዘመድም ያለሽ ዛሬም እዚያ ነሽ!" ይሉ ነበር።ከዚህ ሌላ እንጂኔር ይበልጣልን በስልክ ሁለቴ አነጋግሬ አለሁ። ቡርቱካን ሚደቅሳን አሁንም አነጋግራታለሁ። በጥሞና እነደተሳታፊ፤እንደህግ ባለሙያም ያኔ የሆነውን፣ለእስራትና ለስደት ያበቃትን ከሁለት ዓመት በፊት አውግታኛለች።ከልጆቼ እንደአንዱ አያታለሁ። ልደቱን በካል አላውቀውም። የዛሬ ስንተስ አመት (March 8,2006)ምርጫው ውስጥና ውጭ ስለሆነው ነገር የጻፈውን መጽሐፍ አንብቤ ፤ወድጀው፤Email አድርግኄለት መልስም(03/27/2006) ስጥቶኛል።እውቄቴ ይህችው ነች!

የአሁኑ ውዝግብ ዘመነ ደርግን ያስታውሰኛል።በየቀኑም ባይሆን በየሳምንቱ አዲስ ድርጀት ወይም ስንጣቂ ተመሥርቶ ወረቀት ይበትንና ያንን አገኘው ነበር። የሚደራጅ ሳይሆን የሚፈለፈሉ የሚመስል ነገር ነበረውና "ማለቂያ የለውምእንዴ!" የሚያሰኝ ነገር ነበረው። እንዳያልቅ የለምና እንዳይሆን ሁኖ አለቀ። ከዚያ ዘመን  ዛሬም ቢሆን፣አልፎ አልፎ፣ "አለና!" የሚሉና ሙሾ የሚያወረዱ "በቁሙ የሞቱ!" አያለሁ፤ እሰማለሁም። እኔ የማስታውሰው የመጨረሻው "የሰንጥቅ" ደርጅት መሥራች ዶክተር አለሙ አበበ መስለኝ። "ቀይ ባንዲራ!" ነው ያለው? የመኢሶን ግንባር ተዋናይ ነበርና መኢሶን ላይ ጀንበር ሲያዘቀዝቅ ሲ አይቶ መስለኝ ቀይ ባንዲራ ያነሳው።ለሱም አልበጀውምና ከርቸሌ ወረደ።

ለምንውቀውም ለማናወቀውም ዝርዝሩ ብዙ ነውና አልገባበትም።ብፈልግም የምችል አይመስለኝም። አልበርት አይንስታይን(Albert Eienstein) ብሏል ያሉትን እደግማለህ።"ያንኑ እየመላለስ ግን ከቅድሙ የተለየ ወጤት አገኛለሁ ብሎ የሚያምን እብድ ብቻ ነው!"የኛም ሰው ይህንኑ ይላል። "አብዷል እንዴ!  አብዳለች እንዴ!"  ይህንን የሚሉት ተመክሮም ተዘክሮም የማይመለስ ሰው ሲያገኙ ነው።

አሁኑ ያሉት ድርጅቶች ከሌላው አለም ተምክሮ አለመማመር ብቻ ሳይሆን ባለፈው 50 አመታት በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ ከሆነውም አልተማሩም። ከሌላው ስህተት አለመማመር ብቻ ሳይሆን ተትላንት ጥዋት ራሳቸው ከስረሩትም የተማሩ አልመስለኝም። አንድ ሌላነገር፤ ከወጣንበት፤ ከመጣንበት፣ የተሻለ ቀንም እናመጣልህለን ከምንለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ የአኗኗርና የአደረጃጀት ታሪክም የምንማር አለመስለኝም።ኢትዮጵያ ውስጥ ለምሳሌ ያክል እቁብና እድርን እንውሰድ።የአንድ እቁብ ወይም እድር ዳናኛ "እባክችሁ ደክሞኛልና ሌላ ዳኛ እንፈልግ!" ብሎ  ለምኖ ነው ከዳኝነቱ የሚነሳው። ከሥልጣኑ ማለት ነው!!ከዚህ የምንማረው ቢኖር ጀማው፤የእድሩ ወይም የእቁቡ አባላት በዳናቸው ላይ ሙሉ እምነት አላቸው ማለት ነው። ይህንን ማለት ደግሞ መጀመሪያውኑ የሚሆናቸውን፤የሚያዘልቃቸውን ሰው አይተውና ፤ለየተው መርጠው ነበር ማለት ነው።

ይህ  በየሳምንቱ የፖለቲካ ድርጅት መሪ መለዋወጥ የሚያመጣው ሌላም ችግር ያለው ይመስለኛል።የድርጅቱን ተቀባይነት ያሳጣል። አንድ የሕዝብ ስበስባ ላይ ባለፈው ሰኞ አሰፋ መሪ ነኝ ብሎ መጥቶ የአሁኑ ሰኞ ከበደ መሪ ነኝ ብሎ ቢመጣ ሕዝቡ ግራ

የሚጋባ ይየመስለኛል። “ስምህን ማን አለከኝ? ያ አስፋ የተባለው ሰውዬ አልነበር አሊቃችህ?” የሚልና የመሳሰለ ጥያቄ ያስነሳል። የመሪና የድርጀት ስም አብሮ አጣምሮ ማየትና ማወቅ አለ::Name Recoginition የሚሉት ነው። ይህ በተለዋወጠ ቁጥር ሕዝቡ፤ደጋፊ የሆነውም ያለሆነውም ይህንን ነገር “የልጅ ጫወታ አደርጉት እንዴ?” ማለቱ የማይቀር ነው። እኔም እላለሁና!

የኦርቶዶክሱ ካሕን ሲያሳርግ በሚለው ልቋጭ መስለኝ።”ዘሀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት !” ይላል። “ላለፈው ምህርትን ለመጨው መቆጠብን ይስጣችህ!” ማለት ነው። መቆጠብ ማለት ደግሞ ያንኑ አለመደጋገም ማለት ነው

ካህናቱ “ገዝቻለሁ!” የሚሉትም አላቸውለ። የህ የሚሆነው ተመክሮ ተዘክሮ አልመለስ ያለውን ዳግም እዚያች ቦታ/ ድርጊት ድርሽ እንዳትል ብሎ ቁልፍ መቆለፍ ማለት ነው። መጽሐፉ ውስጥ “ያሰራችሁት የታሰረ የፈታችሁት የተፈታ ይሁን” የሚል ሥልጣን ተሰጥቷቸዋልና ነው።

አወይ ያ ሥልጣን ቢኖረኝ!